Sanctions Practitioners
Compliance Trainers

Compliance & Capacity Skills International, LLC

24 ሴፕቴምበር 2018

# የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማእቀቦች እና የአፍሪካ ድንበር ቁጥጥር ባለስልጣናት

በቶማስ ቢፍዎሊ /Thomas Bifwoli/

## መግቢያ

የጉምሩክ እና ድንበር ቁጥጥር ሰራተኞች በእያንዳንዱ ሀገር ውስጥ ድንበር ዘልል የሆነን ህገወጥ ንግድ ለመቆጣጠር የመጀመሪያዎቹ የመከላከያ መስመሮች ናቸው ይህም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በሰሜን ኮሪያ ጦር መሳሪያዎች እና ጦር ሀይል ግብአቶች ላይ የጫነውን ማእቀብ እና እግድ ማስከበርምን ጨምሮ ነው። ቢሆንም የአፍሪካ ጉምሩክ ባለስልጣናት ከድንበር ጥበቃ ይልቅ ገቢ ማሳደግ ላይ ትኩረት እንደሚያደርጉ ታይቷል። እንደ ኬንያ፣ ኡጋንዳ፣ ታናዛኒያ፣ ሩዋንዳ እና ብሩንዲ ያሉ የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ ሀገራት እያንዳንዳቸው የሀገር ውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ ስልጣን ያላቸው ተቋማታቸው ያሉት (የሀገር ውስጥ ገቢ እና ጉምሩክ) በአንድ መስሪያ ቤት ስር ነው።[1] የሀገር ውስጥ ገቢ ስብሰባው በእያንዳንዱ የ EAC ሀገራት የምጣኔ ሀብት እድገት ላይ የሚመሰረት ነው። ይህ በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ያለ ነባራዊ ሁኔታ ነው። ምሳሌ ሊሆነን የሚችለው የሀገር ውስጥ ገቢዎችን እና የጉምሩክ ክፍያዎችን የመሰብሰብ ሀላፊነት የተጣለበት የኢትዮጲያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው። አዚህ ጋር ያለው ጉዳይ እነዚህ ኢኮኖሚዎች በተለያየ የእንቅስቃሴ ከባቢ ውስጥ መሆናቸው ነው። እንዳንድ የ EAC ሀገራት፣ ልክ እንደአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ኢኮኖሚዎች፣ ከዋናዎቹ መካከል እንደ የእርስ በርስ ጦርነት፣ ከቁጥጥር ውጪ የሆነ ግሽበት፣ እንዲሁም የሀገር ውስጥ ገቢ ላይ ትልቅ ጫና በሚያሳድረው ከፍተኛ የሆነ የውጪ ምንዛሬ ተመን መለዋወጥ የሚጠቁ ናቸው።

በ 2014/2015፣ የበጀት አመት ሁሉም በ EAC ክልል ውስጥ ያሉ የገቢ ባለስልጣናት (RA) ከበፊት አመታት ይልቅ በመጠኑ ከፍ ያለ ገቢ እንደሚከተለው ሪፖርት አድርገዋል፡ OBR (የብሩንዲ ገቢ ባለስልጣን) 415.45 ሚሊዮን፣ RRA (የሩዋንዳ ገቢ ባለስልጣን) 1,230.90 ሚሊዮን፣ KRA (የኬንያ ገቢ ባለስልጣን) 11,713.64 ሚሊዮን፣ TRA (የታንዛኒያ ገቢ ባለስልጣን) 6,059.80 ሚሊዮን፣ እና URA (የኡጋንዳ ገቢ ባለስልጣን) 3,371.03 ሚሊዮን። እነዚህ ጭማሪዎች በሁሉም RAዎች ውስጥ ቢታዩም፣ OBR እና URA ብቻ ናቸው በየበኩላቸው በ 117.2 እና 101.4% ኢላማቸውን ያለፉት። ሌሎቹ ግባቸውን ማሳካት አልቻሉም።[2]

ገቢ ከመሰብሰብ ተግዳሮት በተጨማሪ፣ የባህር በር ወደሌላቸው ሀገራት የሚላክ እቃ ላይ የትራንዚት ካርጎ ቁጥጥር ማድረግ ለአብዛኛዎቹ ሀገራት እና የጉምሩክ ባለስልጣናቶቻቸው ተግዳሮት ነው። እነዚህ ሀገራት ትኩረታቸው ገቢ መሰብሰብ ላይ ሲሆን፣ ያለው ዳታ ግን በመጀመሪያው መግቢያ ነጥብ ላይ ቀረጥ የማይጣልበት የትራንዚት ካርጎ ጭማሪ እንዳሳየ ነው። እናም የትራንዚት ካርጎ ባረፈበት ሀገር ገበያ ውስጥ ገብቶ እንደማይቀር ማረጋገጥ የሚቻልበት ስልት ማስቀመጥ ያስፈልጋል። በተጨማሪም፣ በትራንዚት ካርጎ ላይ የሚደረግ ዝቅተኛ የሆነ ቁጥጥር በተባበሩት መንግስታት ማእቀብ የተጣለበት እቃ በቀላሉ ከጉምሩክ ቁጥጥር ሊያመልጥ ይችላል ማለት ነው። ከዚህ ቀጥሎ በሞምባሳ በኩል የሚያልፈውን የትራንዚት ካርጎ ምሳሌ እንመልከት።

---

[1] እናም በእያንዳንዱ EAC ሀገር ውስጥ ትኩረት የሚደረግበት ነገር ገቢ ስብሰባ ነው።
[2] በ 2016 ዓ.ም በታተመው የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ንጽጽራዊ የገቢ ትንተና ሪፖርት ላይ የተመሰረተ።

Rico Carisch
rico.carisch@comcapint.com
+1-610-390-9541

www.comcapint.com
110 West 94 Street – 2D
New York, NY 10025

Loraine Rickard-Martin
loraine.rickard-martin@comcapint.com
+1-917-715-2142

| *ሰንጠረዥ፡ በምምባሳ ወደብ በኩል የሚያልፈው የትራንዚት ካርጎ* | | | |
|---|---|---|---|
| መዳረሻ ሀገር | 2017 ዓመተ-ምህረት (በቶን) | 2016 ዓመተ-ምህረት (በቶን) | የትራንዚት ሼር በ% |
| ኡጋንዳ | 7,112,971 | 6,346,715 | 82.3% |
| ደቡብ ሱዳን | 673,752 | 597,852 | 2.8% |
| የኮንጎ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ | 360,124 | 376,935 | 4.2 |

ሁልጊዜም የሚጨምረው የጉምሩክ ባለስልጣናት ንግድን የማቀላጠፍ እና ገቢ የመሰብሰብ ፍላጎት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማእቀቦችን ለማስከበር በሚደረገው ጥረት ላይ ተግዳሮት የሚያስቀምጥ ነው። አባል ሀገራት አንደ ሽብርተኛነት አይነት አለም አቀፍ ስጋቶችን ውጤታማ በሆነ መንገድ ስለ መቆጣጠራቸው ያለው መረጃ እምብዛም ነው።

## ገቢ መሰብሰብ ከ ድንበር ቁጥጥር

ከጉምሩክ ቀረጦች በሚገኝ የገቢ ስብሰባ ላይ ጥገኞች የሆኑ ሀገራት ምጣኔ ሀብቶች በጉምሩክ አስተዳደራቸው ላይ ገቢ የመሰብሰብ ሀላፊነት ጥለዋል። ይህ እያደጉ ባሉ ሀገራት ውስጥ ይብስ የሚታይ ነው። ያደጉ ሀገራት በሌላ በኩል ድንበር ቁጥጥር ላይ ትኩረት ሲያደርጉ ይታያል በተለይም በወጪ ንግድ እና ገቢ ንግድ እገዶች ላይ።[4] በአውሮፓ ሕብረት ውስጥ ለምሳሌ፣ እቃዎች ድንበሮችን አልፈው በቀላሉ መንቀሳቀስ የሚችሉ ሲሆን በሀገራቱ የጉምሩክ ኤጀንሲዎች ዝቅተኛ የሆነ ገቢ ነው የሚሰበሰብባቸው። በቅርብ ጊዜ ውስጥ በአለም አቀፍ ነጻ ንግድ እና አለም አቀፍ ሽብርተኛነት ላይ የታየው መጨመር በብዙ ምጣኔ ሀብቶች ውስጥ በድንበር ቁጥጥር እና ደህንነት ቅድሚያ ተሰጥቶበታል። በ EAC ውስጥ ጥምረት ያለው ጉምሩክ ታስቦ ነበር (ይህም በ 1999 ዓ.ም ስምንት ላይ እንደገና ቀርቦ ነበር[5])፣ እንዲሁም በዚህ የንግድ ክልል ውስጥ ነጻ የሆነ የእቃዎች እቅስቃሴ ያለ ሲሆን በተለይም በ 2013 ዓ.ም አንድ የጉምሩክ ክልል ስራ ከተጀመረ በኋላ ነው።[6] ነገር ግን፣ የጉምሩክ ባለስልጣናት በዋናነት የተቀመጡት ገቢ ለመሰብሰብ ነው። ተመሳሳይ ክልላዊ የንግድ ስምምነቶችም ተፈርመዋል። እንደ ምሳሌ፣ አፊሴላዊ ያልሆነው የድንበር ዘለል ንግድ (ICBT) እና ድንበር ዘለል ደህንነት አስተዳደር (CBSG) በጁን 2018 ዓ.ም ላይ ተፈርመው ነበር ይህም በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በየነ መንግሥታት ባለስልጣን (IGAD) አባላት ክልል ነው።[7] ይህ እንቅስቃሴ በ IGAD አባል ሀገራት ድንበር ዘለል ንግድ ላይ የተሻለ አስተዳደር ይኖር ዘንድ ነው

በ EAC RAዎች የሀገር ውስጥ ገቢን ለማሳደግ የተደረገው ጥረት እንዳለ ሆኖ የጉምሩክ ገቢ ስብሰባ ከጠቅላላ የታክስ ገቢዎች በእጅጉ በልጦ ይታያል። ይህ በ EAC ውስጥ ያሉ መንግስታት የክልላዊ ንግድ እና አለም አቀፍ ንግድ ጥምረትን ለመፍጠር ያላቸውን ፍላጎት የሚያንጸባርቅ አይደለም። እነዚህ ሀገራት ጠባብ የሆነ የሀገር ውስጥ ቀረጥ መሰረት ያላቸው ስለሆኑ በተደጋጋመ በጉምሩክ ገቢ ላይ ጥገኞች ሲሆኑ ይታያል። ይህም መጠኑ ትልቅ በሆነው ድብቅ ኢኮኖሚ እና የጥሬ ገንዘብ ኢኮኖሚ ሲሆን ለገቢ ስብሰባ ትልቅ የሆነ ተግዳሮት ነው።

ተነጻጻሪ ቁጥሮች (የጉምሩክ ስብሰባ) ለእያንዳንዱ የገቢ ባለስልጣን እንደሚከተለው ነው፡ ለሁለቱ 2014/15 አመቶች፣ የኡጋንዳ ገቢ ባለስልጣን (URA) የጉምሩክ ገቢውን ድርሻ 42% ላይ አድርጎ ቆይቷል፣ ይህም ከ 2013/14 ጋር ተመሳሳይ

---

[3] ምንጭ የኬንያ ወደቦች ባለስልጣን ኮርፖሬት ዳታ።

[4] ዴቪድ ዊዶውሰን፤ የጉምሩክ ተለዋዋጭ ሚና እድገት እና ዝግመተ ለውጥ። የአለም የጉምሩክ መጽሄት፣ እትም 1 ቁጥር 1 ገጽ 31

[5] EAC የተመሰረተው በ 1967 ዓ.ም፣ ሲሆን በ 1977 ዓ.ም ፈርሶ እንደገና በ 1999 ዓ.ም መልሶ ተቋቋመ። የጋራ ገበያ፣ የጉምሩክ ህብረት፣ የገንዘብ ህብረት፣ እና ፖለቲካዊ ፌደሬሽን የቅርብ የሆነው ስምምነት ዋና ዋና ባህሪያት ናቸው።

[6] የአንድ ጉምሩክ ክልል (SCT) "ፈቃደኞች በሆኑ" ሀገራት ተመልሶ እንዲመጣ የተደረገ ሲሆን በዋናነት "ኬንያ፣ ኡጋንዳ እና ሩዋንዳ በኋላ ደግሞ ብሩንዲ አና ታንዛኒያን ጨምሮ ነው -- ይህም በ 1999 ዓ.ም የ EAC ውል ታስቦ የነበረውን የጉምሩክ ህብረት ለማስጀመር ነው።

[7] የ IGAD ሀገራት ኬንያ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጲያ፣ ሱዳን ደቡብ ሱዳን፣ ኡጋንዳ እና ሶማሊያን ያካትታል።

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር፡ (610) 390 9541 2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York, NY 10025 loraine.rickard-martin@comcapint.com

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715

ሲሆን፣ የኬንያ ገቢዎች ባለስልጣን (KRA) ግን መጠነኛ የሆነ የአለም አቀፍ ቀረጥ መቀነስ ታይቶበታል፣ ይህም 32.5% የነበረ ሲሆን በ 2013/14 ከነበረው 33.3% አንጻር ማለት ነው፣ በሩዋንዳ ገቢዎች ባለስልጣን (RRA) በ 2014/15 30.8% የነበረው በፊት ከነበረው አመት 31.7% ጋር ይነጻጸራል እንዲሁም የብሩንዲ ገቢዎች ባለስልጣን (OBR) በ 2014/15 የመዘገበው 34.7% ሲሆን በ 2013/14 ከመዘገበው 37.0% ጋር የሚነጻጸር ነው። በታንዛኒያ ገቢዎች ባለስልጣን (TRA) ከተመዘገበው ጠቅላላ የግብር መጠን የጉምሩክ ድርሻ በ 2013/14 ከነበረው 36.7 ወደ 38.8 ከፍ ሊል ችሏል።

ከላይ ያለው ውጤት በ EAC ሀገራት ውስጥ የጉምሩክ መስሪያ ቤቶች ገቢ ከመሰብሰብ አንጻር ያላቸውን ወሳኝ ሚና ያሳያል። ለምሳሌ፣ በኬንያ ውስጥ ለአንዳንድ የጉምሩክ ባለስልጣናት የሚሰጠው ስልጠና ገቢን ከማሻሻል አንጻር ነው። ብዙ የሆኑ ምሳሌዎች መኮንኖች ስለ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማእቀቦች ምንም እውቀት እንደሌላቸው የሚያሳዩ ሲሆን በዚህም ምክንያት የህገወጥ ንግድ አጋጣሚዎችን የመለየት አቅም ይጎድላቸዋል። በቅርብ ጊዜ ውስጥ በተለያዩ አፍሪካ ሀገራት ውስጥ የጉምሩክ አገልግሎትን ራስ-ሰር የማድረግ ሙከራ ይታያል፣ አላማቸውም በድንበር ደህንነት ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ ንግድን ማቀላጠፍ እና ገቢ በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ ያሉ ክፍተቶችን ወደ መዝጋት ያዘነበሉ ናቸው። እነዚህም የጉምሩክ መስሪያ ቤቶችን ምርታማነት እና ስራዎችን የሚያቀላጥፍ፣ ሙስናን የሚቀንስ፣ እንዲሁም የመንግስት ገቢን ሊያሳድጉ የሚችሉ ግምትን የሚያሻሽሉ ሲስተሞች ግዢን ያካትታሉ። እነዚህ ሲስተሞች በሕገ ወጥ መንገድ ዕቃዎችን ማስረግን በመቀነስ እና በድንበር ዘለል ንግድ ላይ የሚደረጉ ህጋዊ ያልሆኑ/ኮንትሮባንዶች ፍሰት ቁጥጥር ላይ እምብዛም ትኩረት የላቸውም።

በብሄራዊም ሆነ በክልሎች ደረጃ በተባበሩት መንግስታት ማእቀብ የተጣለባቸው ሀገራት የሚያደርጉትን ህገወጥ ንግድ ለማስቀረት የሚያስችል ሲስተም እና መሳሪያዎችን የአፍሪካ ሀገራት የጉምሩክ መስሪያ ቤቶች ሊያስቀምጡ ያስፈልጋል። የአፍሪካ ህብረት በተለያዩ ጊዜዎች፣ አባል ሀገራት እንደነዚህ ሀገራት እንዴት አድርገው የተሻለ የድንበር ቁጥጥር ማድረግ እንደሚችሉ የሚያሳውቅ እርዳታ ለማድረግ ሞክሯል።[8] የነዚህን ጥረቶች ውጤት የሚያሳይ ምንም አይነት የተጠናቀረ ጥናት ማስረጃ የለም። ግልጽ የሆነው ነገር ብዙ ሀገራት ድንበራቸውን በመቆጣጠር ሂደት ውስጥ ተግዳሮት እንዳለባቸው ሲሆን ይህም በተለያዩ ጥናቶች የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የ DPRK ልዩ ባለሞያዎች ሪፖርትንም ጨምሮ ነው። በተለያዩ ሀገራት ከሰሜን ኮሪያ ጋር በሚያደርጉት ንግድ ላይ አብዛኛውን ጊዜ እገዳ ያለባቸው የጦር መሳርያዎች አፍሪካ ሀገራት ውስጥ እንደሚገቡ እንዲሁም ሌሎች ሸቀጦች ደግሞ ወደ DPRK እንደሚላክ ታውቋል።

በተወሰነ መንገድ የእነዚህ የማስከበር አለመሳካቶች ምክንያት የአፍሪካ ድንበር ቁጥጥር ድርጅቶች ትኩረት ገቢን ማሳደገ ላይ በመሆኑ ነው። ነገር ግን፣ እነዚህንም አላማዎች ጨምሮ፣ የ EAC ሀገራት የተቀመጡ የገቢ ግቦችን ማሳካት ላይ ተግዳሮቶች አለባቸው ይህም አንደሚከተለው ነው:

1. አንደ ምስራቅ አፍሪካ ገቢዎች ባለስልጣናት ቴክኒካዊ ኮሚቴ የ 2016 ሪፖርት፣ ከዋናዎቹ ተግዳሮቶች ውስጥ እንደኛው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣውን መደበኛ ያልሆነ ዘርፍ እንዴት መቋቋም ይቻላል የሚለው ነው። ይህ እድገት፣ በዋናነት ሰፊ ወደ ሆነ የግብር መሰረት ሊቀየር ያስፈልጋል ይህም የሚሰበሰበውን ገቢ ያሳድገዋል። ነገር ግን፣ አሁን በዚህ ዘርፍ ላይ ያሉት ተግዳሮቶች እንደ ቡክ ኪፒንግ እና የገንዘብ አስተዳደር ክህሎት፣ አይነት መሰረታዊ ጉዳዮች ሲሆኑ በተጨማሪም ተሳታፊዎችም ከአንድ ዘርፍ ወደሌላው በየጊዜም መቀያየራቸውም ሌላው ችግር ነው። አብዛኛዎቹ RAዎች አነዚህን ለመቆጣጠር የሚያስችል አቅም ላይ አይደሉም።

2. ሁለተኛው ጉዳይ አቅም ግንባታ ነው። በዚሁ (EACRATC of 2016) ሪፖርት ላይ በሁሉም ገቢዎች ባለስልጣናት ዘንድ አቅምን መገንባት ተግዳሮት እንደሆነ ታይቷል። ለምሳሌ፣ በ OBR፣ ውስጥ አዳዲስ ሰራተኞች ቀጣይነት ያለው ስልጠና እንደሚያስፈልጋቸው ነገር ግን ይህን ለማድረግ ምንም አይነት ግብአት እንደሌለ ታይቷል። በሌሎች ገቢዎች ባለስልጣናት፣ ለምሳሌ በ TRA፣ ውስጥ ግብር ከፋዮችን ኦዲት የማድረግ መሰረታዊ ክህሎት እጥረት ያለ ሲሆን በተጨማሪም እንደ "ቴሌኮምኒኬሽን፣ የፋይናንስ አገልግሎት፣ ነዳጅ፣ ጋዝ፣ ማእድን ቁፋሮ እና ቱሪዝም" ያሉት ላይ የክህሎት እጥረት አለ።

[8] በአፍሪካ ህብረት የተሰሩ ክልላዊ ትብበሮችን በቅጥያው ላይ ይመልከቱ።

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር: (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York, NY 10025 loraine.rickard-martin@comcapint.com

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር: (917) 715

3. ሶስተኛ፣ የግብር ፖሊሲ መጽደቅ ላይ መዘግየት እና/ወይም RA ዋናውን ግባቸውን፣ ማለትም ገቢ መሰብሰብ ላይ ያላቸውን ግብ ለማሳካት አሁን ያሉ ፖሊሲዎችን ለማሻሻል ምን መደረግ እንዳለበት በቂ እውቀት አለመኖር። በመላው EAC RA ከ (EACRATC ሪፖርት) እንደታየው አንዳንድ እየተተገበሩ ያሉ ፖሊሲዎች ምክንያታዊ ባልሆነ መንገድ የሚዘገዩ ሲሆን፣ አንዳንዴም በቀጥታ ውድቅ ይደረጋሉ፣ ይህም ገቢ የመሰብሰብ አላማ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

## የተደረጉ ለውጦች እና የድንበር ቁጥጥር ተግዳሮቶች

አፍሪካ 109 አለም አቀፍ ድንበሮች ያላት ሲሆን ጠቅላላ ርዝመቱም 45,000 ኪሎሜትር ይሆናል። ከእነዚህ ድንበሮች ውስጥ በግልጽ ምልክት የተደረገባቸው ከ 35% በታች ናቸው። የአፍሪካ ድንበሮች በከፍተኛ የመጣስ እና ደካማ አስተዳደራቸው የሚታወቁ ናቸው።[9] ይህም ጉዳይ ሁሉም አይነት ድንበር ዘለል የወንጀል ስራዎች እንዲሰሩ የሚያደርግ ነው። በተጨማሪም የአፍሪካ ሀገራት የስልት ለውጥ እንዲያደርጉም ጥሪ የሚያደርግ ነው፣ ምንክያቱም ድንበሮችን የመጠበቅ ሃላፊነት የየሀገራቱ ስለሆነ ማለት ነው።

አውቶሜሽንን ጨምሮ RAዎች ያለባቸውን ተግዳሮት የሚያቀልሉ ሙከራዎች ተደርገዋል፣ ነገር ግን RAዎች ያለባቸውን ተግዳሮት ለመፍታት ተጨማሪ ጥረት ሊደረግ ያስፈልጋል። ከላይ እንደተብራራው፣ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ትኩረታቸው ገቢ መሰብሰብ ሲሆን፣ ድንበር እና ሌሎች የቁጥጥር ስራዎችን መስራት ቀርቶ ይህንን ግባቸውን የማሳካት ችግርም አለባቸው። በተጨማሪም፣ በአብዛኛዎቹ የአፍሪካ ሀገራት የድንበር አስተዳደር ማጣጣም እና ጥምረት ላይ ዝቅተኛ የሆነ ስኬት ነው ያለው።[10]

ከዚህ በታች ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራባቸው የአፍሪካ ሀገራትን የድንበር ቁጥጥር ችግሮችን በሚከተሉት መንገዶች የሚቀርፉ እይታዎች ይገኛሉ፡ 1) የገቢ ግቦችን ማሳካት እና፤ 2) የድንበር ቁጥጥር ችገሮችን መፍታት ይህም የሚመለከታቸው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማእቀቦችን ማስከበርን ጨምሮ።

## በድንበር ቁጥጥር ላይ ያሉ ጉዳዮች/ተግዳሮቶች እና መፍትሄዎች

ከዚህ በታች ያሉት ጉዳዮች በአብዛኛው የአፍሪካ ሀገራትን የሚጎዱ ሲሆን በሌሎች ታዳጊ ሀገራትም ውስጥ ሊኖሩ ይችላሉ። እነዚህም ከአብዛኛዎቹ ውስጥ፣ ማእቀቦችን ውጤታማ በሆነ መንገድ መቆጣጠርን እየጎዱ ያሉ ዋንኛ ተግዳሮቶች ናቸው።

### 1. በድንበሮች ላይ የማስፈጸም ዘዴዎች አለመኖር እና ደካማ የሆነ መሰረተ ልማት (መንገዶች ወዘተ.)

አፍረካ ውስጥ ባሉ አብዛኛዎቹ ሀገራት፣ ብዙ ድንበሮች እና ክልሎች የሚገኙት በጣም ገጠራማ እና የነዋሪ ቁጥራቸው ትንሽ በሆኑ ቦታዎች ነው፣ ይህም ውጤታማ በሆነ መንገድ ቁጥጥር ማድረግ እንዳይቻል ያደርጋል። በእነዚህ ሀገራት ውስጥ፣ የድንበር ቁጥጥር እና ማስፈጸም በዋናነት ትኩረት የሚያደርገው በመግቢያ ወደቦች እና ሌሎች ዋና መግቢያ ነጥቦች ላይ ነው። በሌሎች ትንንሽ መግቢያ ነጥቦች ላይ የሚደረገው ትኩረት አናሳ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ ለኮንትሮባንድ እና እገዳ ለተጣለባቸው ቁሳቁሶች ጥቅም የሚውሉት እነዚህ ናቸው። በተጨማሪም፣ የድንበር እና ጉምሩክ ባለስልጣናት አብዛኛውን ጊዜ እነዚህን ቦታዎች ለማስተዳደር የሚያስፈልጉ ኃብቶች የላቸውም ይህም ህገወጥ ድንበር ዘለል ንግድ ቀላል እንዲሆን ያደርገዋል።

ብዙ የሚታወቁ መደበኛ ያልሆኑ ወይም ህገወጥ መሻገሪያዎች ያሉ ሲሆን ምንም ቁጥጥር አይደረግባቸውም ወይም ደካም ቁጥጥር ነው ያላቸው። ድንበር የሚያቋርጡ የተወሰኑ መንገዶች፣ ለምሳሌ፣ ውስን ወይም ምንም አይነት የጉምሩም

---

[9] የአፍሪካ ህብረት የድንበር ፕሮግራም አዲስ አበባ፣ 2012 ዓ.ም

[10] Ibid

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር: (610) 390 9541 2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York, NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር: (917) 715
loraine.rickard-martin@comcapint.com

ኬላዎች/ቢሮዎች/ጣቢያዎች የሌላቸው ናቸው። ድንበር ላይ ያሉ ቁጥጥሮች እና በድንበር ኬላዎች መካከል ያሉ ቁጥጥሮች መደበኛ ያልሆኑ፣ ዝቅተኛ አቅም ያላቸው እና በቂ ግብአት የሌላቸው ናቸው። አሁን ያሉት ዘዴዎች ህገወጥ የሆነ የእቃዎች እና ሰዎች ዝውውር ላይ ዝቅተኛ የሆነ ቁጥጥር የሚያደርግ ነው።

አብዛኛዎቹ የገጠር ድንበር ኬላዎች በቂ የሰው ሀይል የሌላቸው ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ በቂ የሆነ ውጤታማ የድንበር ቁጥጥር ማድረጊያ መሳሪያዎች ማለትም እንደ ኮምፒውተር፣ ኢንተርኔት፣ የማይቆራረጥ ኤሌክትሪክ እና ለድንበር ተቆጣጣሪዎች መኖሪያ የሚሆን በቂ ቦታ፣ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በቂ የሆነ የብርበራ እና የመጋዘን ፋሲሊቲ የላቸውም።

ትክክለኛው መሰረተ ልማት ማለትም እንደ መለያ መሳሪያ፣ እና ስካነሮች አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ኬላዎች ላይ የሉም፣ ይህም ህገወጥ የሆኑ እቃዎችን ዝውውር ማወቅ አስቸጋሪ ስለሚሆን በሕገ ወጥ መንገድ ዕቃዎችን ለማስረግ መንገዶችን ይከፍታል። የእነዚህ ቦታዎች ገጠር ላይ መሆን በትክክለኛው ሰአት ላይ ትክክለኛው መረጃ እንዳይደርስ እና ማስፈጸም ስኬታማ እንዳይሆን ያደርገዋል።

## 2. የሰራተኞች ቁጥር ማነስ እና ደካማ ስልጠና

በቁጥር 1 ካለው ነጥብ ጋር በሚገናኝ መልኩ ውጤታማ ቅኝቶችን ጨምሮ፣ ከባድ የስራ ጫናን ለመቋቋም በቂ ያልሆነ የሰራተኞች ቁጥር። ካርጎ እንዲያዝ ቢፈለግም እነዚህ ሁኔታዎች በማረጋገጫ ላይ ዝቅተኛ የሆነ ትክክለኛነት እንዲኖር ያደርጋሉ። ይህም ችግር በደካማ አውቶሜሽን ይበልጥ የሚጎላ ሲሆን ስራዎች ማንዋል በሆነ መንገድ እንዲሰሩ ያደርጋል። የሀገራት ድንበር ቁጥጥር ሰራተኞች አብዛኛውን ጊዜ ላለው የተግዳሮት መጠን ቁጥራቸው ጥቂት፣ በቂ ስልጠና የሌላቸው፣ በቂ መሳሪያ የሌላቸው ሲሆኑ ቦታቸው ደግሞ ገጠራማ በመሆኑ ምክንያት ለድርጊታቸው ጥቂት የሆነ ተጠያቂነት ነው ያላቸው።

የሀገሩን ድንበር እንዲጠብቁ ስልጣን የተሰጣቸው የድንበር ሰራተኞች ስራቸውን በብቃት ለመወጣት የሚያስችል በቂ የሆነ አቅም የላቸውም። ይህ አሁን ያለው ሁኔታ የአብዛኞቹ ሀገራት ሁኔታ ነው። ይህም እንደ ደቡብ ሱዳን፣ ባሉ ግጭት ባለባቸው ሀገራት ውስጥ ይበልጥ ከፍ ያለ ነው። የቢሮ ቦታ ማነስ፣ እና የድንበር ተቆጣጣሪዎች መኖሪያ በቂ አለመሆን፣ በቂ ካልሆኑ የመገናኛ መሳሪያዎች ጋር ተደምረው የእነዚህን ሰዎች ስራቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ የማከናወን አቅም እጅጉን የሚፈትን ነው። በቂ ያልሆነ ክህሎት እና የስራ ሀላፊነትን አለመረዳት የተንሰራፉ ተጨማሪ ችግሮች ናቸው። እነዚህን ችግሮች ይበልጥ የሚያባብሰው የጉምሩክ ሕጎችን፣ ክልላዊ ስምምነቶችን እና ለዚህ ስራ ውጤታማነት አስፈላጊ የሆኑ አለምአቀፍ የንግድ ስምምነቶችን ማለትም እንደ ማእቀቦች ያሉትን አለማወቅ ነው።

ለሰራተኞች የሚሰጡት አጭር ስልጠናዎች በጉምሩክ ዲፓርትመንቶች ውስጥ ለመስራት የሚያስፈልገውን ክህሎት አይሰጣቸውም። ከ EAC አባል ሀገራት ውስጥ በአንዱ ለምሳሌ፣ አንድ የጉምሩክ መኮንን የጉምሩክ ዋጋን መተመን ሳይችል ቀርቶ እንደነበር ይታያል (ይህም ወጪን፣ ኢንሹራንስን እና የጭነት መጠንን የሚያካትት ነው)። ለድንበር ቁጥጥር ሰራተኞች ቀጣይነት ያለው ስልጠና ያስፈልጋል። ተለይተው የታወቁ ስልጠናዎች፣ መረጃ ሰጪዎችን መሰብሰብ እና መያዝ፣ የብርበራ ዘዴዎች፣ የምልከታ እና መረጃ ስብሰባ ዘዴዎች እና የወንጀል ሂደቶችን እና ስታቲስቲክስን መረዳት እና መተርጎምን ያካትታል።

በሁሉም ሰራተኞች በድንበር ኬላዎች ላይ ልዩ የሆኑ መሳሪያዎችን መጠቀም የተለመደ መሆን አለበት። የኮምፒውተር ክህሎት እና ሁሉም ሰራተኞች ኮምፒውተር አግኝተው ኔትዎርክ ውስጥ መግባት መቻላቸው ህገወጥ እና የተከከሉ እቃዎችን ለመለየት በሚደረገው ጥረት ላይ ትልቅ ስኬት እንዲኖር ያደርጋል።

## 3. ዝቅተኛ አውቶሜሽን

አውቶሜት የተደረጉ የጉምሩክ ሲስተሞች ወሳኝ የሆነን መሳሪያ ለተጨማሪ ግልጽነት ማለትም ሀላፊነትን መወጣት እና ግብር፣ የጉምሩክ ሂደትን ለመጨረስ በሚደረገው ሂደት ውስጥ የሚያስፈልገውን ጊዜ መቀነስ እና ህገወጥ/የተከለከሉ እቃዎችን ለመለየት ይረዳሉ። በአንድ ሀገር ውስጥ ያለው የጉምሩ ሂደት አውቶሜሽን ከፍ ባለ ቁጥር፣ ዝርዝር የሆነን ቁጥጥር፣ ማጭበርበርን መለየት እና ክስን ጨምሮ ጠንካራ እርምጃ መውሰድ እንዲቻል ያስችላል።

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር፡ (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com
www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York, NY 10025 loraine.rickard-martin@comcapint.com
Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715

ድንበር ዘለል ወንጀልን በመከላከል ላይ አዲስ የሆነ ቴክኖሎጂን ማስተዋወቅ ለአፍሪካ መንግስታት ቅድሚያ የሚሰጠው ስራ ሊሆን ያስፈልጋል። የድንበር ክልሎች ሰፊ ከመሆናቸው ጋር በተያያዘ፣ የተሻለን ቴክኖሎጂ ማለትም ካሜራ፣ ሮቦቶች እና ስካነሮችን ጥቅም ላይ በማዋል ላይ ትኩረት ሊደረግ ያስፈልጋል።

በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ያሉት የጉምሩክ አስተዳሮች በአብዛኛው ወንጀል የሰሩ ሰዎች፣ አውታረ መረቦቻቸው፣ ምን አይነት እና ምን ያክል መጠን ያላቸው ህገወጥ ሸቀጦች እንደያዙ የሚያሳይ ብሄራዊ የውሂብ ጎታ የተሟላላቸው አይደሉም።

የተቋማት ለውጥ፣ በሰው ሃይል የሚደረጉ የድንበር ቁጥትሮችን ለማገዝ ሰውን የማይጠቀም ቴክኖሎጂ ግዢ እና ስራ ላይ ማዋል፣ ዘመናዊ የሆነ ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል እንዲሁም እንደ ድንበሩ ወቅታዊ ፍላጎት ቀጣይነት ያለው የሰራተኞች ስልጠናን መስጠትም ያስፈልጋል። የአፍሪካ መንግስታት ሁሉን አቀፍ የሆነ የመረጃ ማጠናቀሪያ ሲስተሞች በሕገ ወጥ መንገድ ዕቃዎችን ማስረግ ላይ ስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋቸዋል ይህም በሁኔታዎች፣ ቅጦች እና በሕገ ወጥ መንገድ ዕቃዎችን የማስረጊያ መስመሮች ተለዋዋጭ ባህሪ ላይ የመረጃ ስርጭትን ለማቀላጠፍ እንዲሁም የወንጀለኞች የውሂብ ጎታዎችን ለመጀመር ነው።

## 4. ችግር ባለባቸው አካባቢዎች የመንግስት አለመኖር

በአፍሪካ ውስጥ ችግር ባለባቸው አካባቢዎች ላይ ባለስልጣናት የሉም ቢኖሩም እንኳን ምላሽ የሚሰጡ አይደሉም። በማሊ ኒጀር እና ቡርኪናፋሶ መካከል ባለው የሊፕታኮ-ጉርማ ድንበር ክልሎች ላይ የተደረገ ጥናት፣ በመንግስት ላይ ትልቅ የሆነ አመኔታ ቢኖርም፣ የደህንነት ስጋቶች በመጀመሪያ የሚፈቱት በባህላዊ የግጭት መቀነሻ መንገዶች ነው፤ ባለስልጣናት ጉዳዩ ውስጥ የሚገቡት እንደመጨረሻ አማራጭ ነው። ይህም የእነዚህ ሀገራት መንግስታት ተሸጋጋሪ ተግዳሮቶችን ለመፍታት የድንበር ማህበረሰቦችን በመጠቀም ራቅ ያሉ የድንበር ክልሎቻቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ መቆጣጠር እንደማይችሉ ነው። ይህም በአፍሪካ ውስጥ የጦር መሳሪያዎች እና የህገወጥ እቃዎች ዝውውር እንዲጨምር አስተዋጽኦ አድርጓል። ድንበሮች ላይ ቁጥጥር የማድረግ ተግዳሮቶች ሽብርተኞች በቀላሉ ድንበር ዘለል የሆኑ ስራዎችን እንዲሰሩ አስችሏቸዋል።

## 5. በመንግስት መስሪያ ቤቶች መካከል ያለ የትብብር እጥረት

በመንግስት ደረጃ፣ እንደ ኢሚግሬሽን፣ ጉምሩክ፣ ፖሊስ እና መረጃ መስሪያ ቤቶች መካከል ያለው ቅንጅት አንዳንድ ጊዜ በጣም ጥቂት ወይም የለም ሊባል የሚችል ነው። በእነዚህ መስሪያ ቤቶች መካከል ያለው ትልቁ ችግር ከድንበር ዘለል ወንጀል ጋር በተያያዘ በቂ የሆነ የመረጃ መጋራት አለመኖር ነው። በእነዚህ የተለያዩ ሕግ አስከባሪ ድርጅቶች ውስጥ ያለው ይህ ከወንጀል ድርጅቶች ወይም የተደራጁ የወንጀል ቡድኖች ጋር የተያያዘ መረጃን አለመጋራት የእነዚህን ህገወጥ እና የተከለሉ እቃዎች የመያዝ የዕለት-ተዕለት እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ ያደናቅፋል። በድንበር ቁጥጥር እና ጉምሩክ ላይ ስራን የሚሰሩ ባለስልጣናት እና ኤጀንሲዎች ብቻቸውን ሆነው ብዙውን ጊዜ በማይደጋገፉ አላማዎች ከሚሰሩት ስራ ይልቅ አንድ ላይ ሆነው ችግሮችን በመፍታት ላይ ሊሰሩ ያስፈልጋል።

በመንግስት ኤጀንሲዎች መካከል የሚደረግ የቅርብ ትብብር ለውጤታማ የድንበር ቁጥጥር ወሳኝ ነው። በጣም ትልቅ የሆነ ርቀት ያለው ድንበር፣ የሰራተኞች በቂ አለመሆን፣ ጠንካራ የሆነ ግንኙነት እና ያሉትን ግብአቶች በተሻለ መንገድ መጠቀም ወሳኝ እዲሆን ያደርጋል። ይህ ግን አፍሪካ ውስጥ ያለው የአብዛኛው የድንበር መስመሮች ሁኔታ አይደለም። በኤጀንሲዎች መካከል ያለው የትብብር እጥረት አነዚህን ወንጀሎች ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት ያዳክማል።

የአፍሪካ መንግስታት የድንበር ደህንነትን ለማሳደግ መረጃዎችን በመቀያየር እና የጋራ ድንበር ቁጥጥሮችን በማድረግ ስራ ላይ በቅርበት ሊሰሩ ያስፈልጋል። ድንበሮችን ለመቆጣጠር የሚያስፈልጉ ጠንካራ ተቋማት አለመኖር ከአካባቢያዊ እና ክልላዊ ትብብሮች ማነስ ጋር ተደምሮ በድንበር ቁጥጥር ላይ የተቆራረጠ ሲስተም እንዲኖር ይህም ለድብቅ ማስተላለፍ እና ሌሎች የድንበር ላይ ወንጀሎች መንገድ የሚከፍት ሆኗል።

በአፍሪካ ሀገራት እና አለም አቀፉ ማህበረሰብ መካከል ያለውን ትብብር ማጠናከር በተለይም ህግን በማስከበር፣ መረጃዎችን በመጋራት፣ ቀጣይነት ያለውን ንግግር እና ስልጠና ማድረግ የድንበር ደህንነትን በማጠናከር ሂደት ላይ ትልቅ ሚና አለው።

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር: (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York, NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር: (917) 715
loraine.rickard-martin@comcapint.com

## 6. የተቀናጀ ወንጀል

የተቀናጀ ወንጀል የተለያዩ መልኮች ሊኖሩት ይችላሉ፣ ከነዚህም መረጃዎችን ለወንጀለኛ ቡድኖች መሸጥ፣ ህገወጥ የሆኑ እቃዎች ዝውውርን ማስቻል እና ምርመራዎችን ማደናቀፍ ይገኙበታል። መረጃን መሸጥ ለወንጀለኛ ቡድኖች መረጃውን መስጠት ይህም እየተካሄዱ ስላሉ ምርመራዎች ወይም ወንጀለኞች ሳይታወቅባቸው እንዲያመልጡ የሚያደርግ የአሰራር መረጃዎችን መስጠትን ያካትታል።

አፍሪካ ውስጥ፣ ህገወጥ እቃዎችን በሕገ ወጥ መንገድ ማስረግ ብዙ ጊዜ ከተደራጀ ወንጀል ጋር ከሚያያዙ የድንበር ዘለል ተግባራት ውስጥ ነው። በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ የድንበር ጠባቂዎች ራሳቸው በሕገ ወጥ መንገድ ዕቃዎችን ማስረግ ውስጥ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይችላሉ። የወንጀል ቡድኖች ተጋላጭነት ያላቸውን መኮንኖች ለመለየት ትልቅ ርቀት እንደሚሄዱ ታውቋል እነዚህም ሰዎች ማጭበርበር ላለበት ስራ ምላሽ የመስጠት እድል ያለው ሲሆኑ ወይም ሙስናን እና ማስፈራራትን በመጠቀም የድንበር ጠበቂዎችን የሚያልፉ ናቸው። የጉምሩክ መኮንኖች በተጨማሪም ለተደራጁ ወንጀለኞች የሀሰት ሽፋንን በመስጠት፣ መረጃዎችን በማጭበርበር እና ሲስተም ውስጥ የሀሰት መረጃን በማስገባት ይሰራሉ። ለማጭበርበር የተጋለጡ ሰነዶች የጭነት መግለጫዎችን፣ የአምራች ሃገር ማስረጃ እና ሌሎች ወደ ሐገር ውስጥ ማስገቢያ ሰነዶችን ያካትታሉ።

በሌሎች ሁኔታዎች ማለትም የድንበር ቁጥጥር ሰራተኞች ኮንትሮባንዶችን በያዙባቸው ሁኔታዎች ላይ፣ ይህንን ስራቸውን ለማደናቀፍ ወንጀለኞች ከከፍተኛ የመንግስት ባለስልጣናት ጋር ትብብር ያደርጋሉ።

እስከ ዛሬ ድረስ እንደዚህ አይነት የተደራጁ የወንጀል ቡድኖችን ጥቅም ላይ በማዋል ከሰሜን ኮሪያ ጋር ምን ያክል ክልከላ የተደረገበት ንግድ በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ ተደርጎ እንደሆነ ግልጽ የሚያደርግ ዳታ የለም።

## 7. ሙስና

የጉምሩክ ስራ ባህሪ በመጀመሪያ መስመር ላይ ላሉ ሰራተኞች ከፍተኛ ሚስጥራዊነትን ይሰጣል። እንዲህ አይነት ሚስጥራዊነት የህገወጥ ንግድ ስራ እንዲሰራ የሚያደርግ እድልን ይከፍታል። ጥሩ የሆነ አቋም ያላቸው የጉምሩክ ሰራተኞች ከሚገጥማቸው ዘርፈ ብዙ ተግዳሮት ጋር በተያያዘ፣ በሰሜን ኮሪያ የጦር መሳሪያዎች ላይ የተጣለውን እግድ ለመከታተል በቂ የሆነ ትኩረት ላይሰጡት ይችላሉ።

ዝቅተኛ የሆነ ክፍያ፣ ከባድ የስራ ሁኔታ፣ እና ዝቅተኛ የሆነ መለየት እድል ለሙስና እድልን ይፈጥራል። በአንዳንድ የአፍሪካ ሀገራት፣ የድንበር ተቆጣጣሪዎች ደሞዝ ከሀገሪቱ የመኖሪያ ደመወዝ በታች ሲሆን አንዳንድ ባለስልጣናት ይህንን ለማካካስ ሙስናን ይጠቀማሉ። በተጨማሪም፣ በድንበር ተቆጣጣሪ እና የጉምሩክ መኮንን መካከል ያለው የደሞዝ ልዩነት እንዲሁም ከሙስና ሊገኝ የሚችለው ገንዘብ እድል ሙስና እንዲፈጠር ዋናው እና ትልቁ ምክንያት ነው።

ሙስና ድንበሮች አንደ ህገወጥ የሰዎች፣ እጾች፣ ትናንሽ ጦር መሳሪያዎች እና ቀላል መሳሪያች ዝውውር በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ እንዲሆኑ እና በቅርብ ጊዜ ውስጥ ደግሞ ሽብርተኛነት እንዲስፋፋም ያደርጋል። እነዚህን ጉዳዮች የሚያባብሱት በቂ የሆነ የሰው ሀይል አለመኖር፣ ውጤታማ በሆነ መንግድ ትብብር የሚያደርግ እና መነሳሳት ያለው ሀይል አለመኖር እንዲሁም ሙስናዎችን ለመሰብሰብ የሚያስችል እድል የሚፈጥርላቸውን ከፍተኛ ሚስጥራዊነት ማግኘት መቻላቸው። የወንጀል ተቋማት አንዳንድ ጊዜ ለፖሊሶች፣ ኢሚግሬሽን፣ እና ጉምሩክ መኮንኖች እጾችን እና ጦር መሳሪያዎችን ሲያዘዋውሩ አንዲሁም በግብር ማጭበርበር ላይ ጆሮ ዳባ ልበስ እንዲሉ ሙስናን ይጠቀማሉ።

## 8. በፖሊሲ እና አፈጻጸም መካከል ያለ ክፍተት

አፍሪካ ውስጥ ያሉ ብዙ ክልላዊ ህብረቶች፣ ምሳሌ የምስራቅ አፍሪካ ማህበረሰብ (EAC)፣ ድንበሮች ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችል ፖሊሲዎችን አርቅቋል። እነዚህም ከመከላከል፣ አስተዳደር እና የግጭት አፈታት መፍትሄ ጋር ተያያዥ የሆኑ ፖሊሲዎችን እና ህገወጥ የእቃዎች ዝውውርን የሚያስቀሩ የተለመዱ አቀራረቦችን የሚያካትት ነው። እነዚህ ጥረቶች የድንበር ቁጥጥርን፣ ፍልሰት እና ሽብርተኝነትን ለመከላከል ያለሙ ናቸው። ከድንበር የሚነሱ ስጋቶችን ለመቀነስ ከእነዚህ

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር፡ (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York, NY 10025

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715
loraine.rickard-martin@comcapint.com

ክልሎች ግንኙነት ያላቸው ድርጅቶች የትብብር እና የቅንጅት ጥያቄዎች ሲቀርቡ ቆይተዋል። ነገር ግን መንግስታት እነዚህን ለመተግበር ያሳዩት ምላሽ የተደበላለቀ ነው ይህም የፖለቲካ እና ግብአቶች በቂ አለመሆን ከምክንያቶቹ ውስጥ አንዱ ነው። ይህም በፖሊሲ እና አፈጻጸም መካከል ክፍተት እንዲኖር አድርጓል።

እነዚህ ፖሊሲዎች አሁን ያለውን ችግር መረዳት እንዳለ ቢያሳዩም፣ እነዚህን ውጤታማ ለማድረግ ትርጉም ያለው ግብዓት ጥቅም ላይ አልዋለም። በድንበር ላይ ያሉ የመንግስት ኤጀንሲዎች ትክክለኛው ስልጠና የሌላቸው ሲሆን በወሳኝ የድንበር ጉዳዮች ላይ እውቀትም የላቸውም። በተጨማሪም፣ መንግስታት በድንበር አካባቢ ያለ እድገት ላይ ትኩረት የላቸውም። ይህም ለተቀናጀ የወንጀል መረብ እና ለሌሎች በክልሉ ውስጥ ለሚንቀሳቀሱ አካላት እድል ፈጥሯል።

በተጨማሪም፣ አፍሪካ ውስጥ ያሉ የድንበር ቁጥጥር ወኪሎች ለሀገራቸው ወታደራዊ ወይም የደህንነት ኃይሎች የሚሆን ከሰሜን ኮሪያ የሚመጣ ጦር መሳሪያ ላይ ያሉ የተባበሩት መንግስታት እግዶችን አያስከብሩም። ምክንያቱም ይህን ማድረግ ተቀባይ የሆነውን ሀገር በብሄራዊ ደህንነት ስጋት ውስጥ ስለሚከተው ነው። ለአብዛኛዎቹ ሀገሮች፣ እንደዚህ አይነት ከተባበሩት መንግስታት ጋር ያለውን የፍላጎት ግጭት መፍታት ከፍተኛ የፖሊሲ ችግር ሲሆን የትኛውም የጉምሩክ መኮንን ይህን ይፈታዋል ማለት ዘበት ነው።

### 9. ወደቦች ላይ ያለ ደካማ ፖሊሲ/ሂደት

አብዛኛዎቹ አፍሪካ ሀገራት ውስጥ ያለው የወደቦች ሂደት ድብቅ ማስተላለፎች እንዲካሄዱ የሚያደርግ ክፍተት አለባቸው። ኬንያ ውስጥ ለምሳሌ፣ ትራንዚት ላይ ናቸው ተብለው ለሚጠቀሱ እቃዎች ወይም ስልጣን የተሰጣቸው ነጋዴዎች የሆኑ አቃዎች 100% ስካን አይደረግባቸውም። ይህም ማለት የጉምሩክ ሰራተኞች ያልተረጋገጠ ካርጎ ሀገር ውስጥ እንዲገባ ያደርጋሉ ማለት ነው። ይህም አንድ ህገወጥ የሆነ ዝውውር እና ሽፋን የሚደረግበት መንገድ ሊሆን ይችላል።

### 10. ሰነዶችን ማጭበርበር

አብዛኛዎቹ የመንግስት ድንበር ወኤጀንሲዎች በኢምፖርት/ኢሚግሬሽን ሰነዶች ላይ ያሉ መረጃዎች ትክክለኛ መሆን አለመሆናቸውን የሚያውቁበት ዘዴ የላቸውም። አፍሪካ ውስጥ ያሉ ተቋማት ትልቁ ተግዳሮት ሀሰተኛ ደረሰኝ፣ ሀሰተኛ ምርቶች፣ ዋጋዎች፣ የኤክስፖርተር ዝርዝር፣ የግብይት ቀን ወዘተ ናቸው። ሌሎች ማጭበርበር የሚደረግባቸው ሰነዶች የአምራች ሃገር ማስረጃ፣ የእሽግ ዝርዝር አና የሰነዶች ትክክለኛነት ማረጋገጫዎች ቅድመ ማረጋገጫ ነው። ይህ ችግር በተጨማሪም በሀገራት መካከል ትብብር ባለመኖሩ ይባባሳል። የሀሰት ሰነዶች ህገወጥ የሆኑ/የተከለከሉ እቃዎቸን በሕገ ወጥ መንገድ ዕቃዎችን ለማስረግ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

### ስለ ቶማስ ቢፍዎሊ /Thomas Bifwoli/

| | |
|---|---|
|  | ቶማስ ቢፍዎሊ ለኬንያ ገቢዎች ባለስልጣን (KRA) የሰራ ሲሆን፤ ከዚህ በፊት ደግሞ ለአለም ጉምሩክ ድርጅት ክልላዊ መረጃ ጉዳይ ማስፈጸም ምስራቅ እና ደበቡ አፍሪካ ቢሮዎች (WCO RILO ESA) ዋና መስሪያ ቤት ምክትል ሆኖ ሰርቷል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ማእቀብ ቁጥጥር ባለሞያዎች ቡድን አስተባባሪ ሆኖ ይሰራል። |

**አባሪ**

የተሻለ የድንበር ቁጥጥር ላይ ያተኮሩ በክልላዊ የኢኮኖሚያዊ ማህበረሰቦች የቀረቡ ውሳኔዎች እና ምክረ ሀሳቦች ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡

- የ SALW በ EAC ክልል ውስጥ ያለውን ስርጭት የመቀነስ ፕሮጀክት፣ በ EAC ጸሀፊ የተጀመረ እና በ GTZ ድጋፍ የሚደረግለት (2006 – 2009)
- የናይሮቢ በግሬት ሌክስ ክልል ውስጥ እና አፍሪካ ቀንድ አካባቢ የትናንሽ ጦር መሳሪያዎች እና ቀላል መሳሪያዎች ዝውውር መከላከል፣ ቁጥጥር እና ቅነሳ ፕሮቶኮል (2004)
- የዳሬ ሰላም አለም አቀፍ በግሬት ሌክስ ክልል ውስጥ ያለው ጣምራ መንግስታትን እና ክልላዊ ትብብርን በደህንነት እና ጥበቃ ዙሪያ ማሳደግ ኮንፍረንስ (ICGLR) (2004)
- በጦር መሳሪያዎች፣ ጥይት እና ሌሎች ግንኙነት ያላቸው መሳሪያዎች ቁጥጥር ላይ የ SADC ፕሮቶኮል (2001)
- በክልላዊ ጸረ ሽብር ስልት ላይ የናንዩኪ የመግባቢያ ሰነድ (2006)
- የአርብቶ አደሮችን ትጥቅ ማስፈታት የ IGAD እንቅስቃሴ (ሜይ 2007)
- በግሬት ሌክስ ክልል ውስጥ የ ICGLR ስምምነት በሰላም እና መረጋጋት ላይ (2006)

Enrico Carisch
ስልክ ቁጥር፡ (610) 390 9541
2142
Rico.carisch@comcapint.com

www.comcapint.com
110 West 94 Street 2-D
New York, NY 10025 loraine.rickard-martin@comcapint.com

Loraine Rickard-Martin
ስልክ ቁጥር፡ (917) 715